በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 240983

ቀን ፡- ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ/ም

**ዳኞች-** እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

**አመልካች፡-** ወ/ሮ በላይነሽ ሺበሺ ስራው - ጠበቃ ሀብታሙ ሁነኛው ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-**
1. ዶ/ር ጌታቸው ፈለቀ ፈይሳ - ጠበቃ ዘውዱ ተሾመ ቀረቡ
2. ወ/ሮ አስናቀች ፈለቀ ፈይሳ - ቀረቡ
3. አቶ ፀጋዮ ፈለቀ ፈይሳ - ቀረቡ
4. አቶ ጌታቸው ዘውዱ
5. አቶ ኤፍሬም ፈለቀ ፈይሳ
6. ወ/ሮ ይልፋሸዋ ፈለቀ ፈይሳ
7. ወ/ሮ ትዕግስት ፈለቀ ፈይሳ
8. ወ/ሮ ወይንሸት ፈለቀ ፈይሳ
9. አቶ ዳንኤል ፈለቀ ፈይሳ
10. አቶ ጥበበ ፈለቀ ፈይሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ የሚስትነት ድርሻ ይለይልኝ የሚል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀናበትን የመጨረሻ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፍርድ ቤቱ በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘትም ከባለቤታቸው አቶ ፈለቀ ፈይሳ ጋር ከ1953 ዓ.ም ጀምሮ በትዳር ሲኖሩ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥጥ 103 የሆነውን ሶስት ክፍል የጭቃ ቤት ሙሉ በሙሉ አፍርሰው አንድ ሳሎን፣ ሁለት መኝታ ቤት፣ አንድ እቃ ቤት እና መፀዳጃ ቤት በበሎኬት በስፋት እና ይዘት ቀድሞ ከተሰራው የተለየ ቤት እና ሰርቪስ ቤቶችን ሰርተው እስክ አሁን ድርስ በይዞታቸው ስር አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን፤ ባለቤታቸው ካረፉ በኋላ ሚስትነታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/1681/2002 ላይ የካቲት 03/2002 ዓ.ም ያረጋገጡ መሆኑን፤ ከሟች ህልፈት በኋላ ተጠሪዎች የሟች የውርስ ሀብት እንዲለይላቸው ይጠይቃሉ ብለው ቢጠብቋቸውም ያልጠየቁ መሆኑን በመጥቀስ ከተጠቀሰው ቤት ላይ የሚስትነት ድርሻቸው እንዲለይላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ክስ የቀረበበት ቤት ሟች በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተረጋገጠ ኑዛዜ ቤቱ በስማቸው ተምዝግቦ የሚገኝ ቢሆን የሰሩት 1ኛ ተጠሪ መሆናቸውን እና ሌሎች ምክንያቶችን ጠቅሰው ሌሎች ወራሾች ጭምር እንዳይጠይቋቸው በኑዛዜ አግደው ያስተላለፉላቸው መሆኑን፤ አመልካች ቀድሞ የነበረን ቤት አፍርሰው በይዘትም ሆነ መጠን ከቀድሞው የተለየ ቤት መስራታቸውን የገለፁ ሀሰት መሆኑን፤ ከዚህ ቀደም የአሁን 5ኛ፣ 7ኛ እና 8ኛ ተጠሪዎች ቤቱ የተላለፈበት ኑዛዜ እንዲሰራላቸው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ቤቱን በኑዛዜው መነሻነት በስማቸው አዙረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ ተረጋግጦ አቤቱታቸው ውድቅ የተደረገ ሲሆን አመልካች አሁን ላይ ያቀረቡት ክስም ተመሳሳይ መሆኑን፤ አመልካች ኑዛዜውን ሳይቃወሙ ኑዛዜው ከተደረገ 18 ዓመት በኋላ እና ሟች ከሞቱ ከ14 ዓመት በኋላ አሁን ላይ ክስ ማቅረባቸው አግባብ ባለመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ባለማቅረባቸው እንዲሁም 6ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ቀርበው መልስ ባለመስጠታቸው የፅሁፍ መልስ የመማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡ የአሁን 4ኛ፣ 5ኛ፣ 7ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በአመልካች ጥያቄ መሰረት ድርሻቸው ተለይቶ ቢወሰንላቸው የማይቃወሙ መሆኑን ገልፀው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ክስ ለመስማት በተያዘው ቀን ቀጠሮም የአሁን 3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በክስ እና መልሱ ላይ ግራ ቀኙ ካከራከረ በኋላ አመልካች ያላቸው ድርሻ ሊለይ ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ ይዞ መዝገቡን ከመረመረ ሐምሌ 29/2014 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በውሳኔውም ክርክር የቀረበበትን ቤት አስመልክቶ ሟች የካቲት 02/1996 ዓ.ም በቁጥር 660/7/96 በተመዘገበ ግልፅ ኑዛዜ ለአሁን በ1ኛ ተጠሪ አስተላለፍው በዚሁ መነሻነት የቤቱ ስም ሃብት በተጠሪ ስም ዞሮ በካርታ ቁጥር የካ/207928/10 ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ ቤቱ የተላለፈበት ኑዛዜ ባልፈረሰበት እና ፀንቶ ባለበት አመልካች በጠየቁት መሰረት የድርሻ ክፍፍል የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም በማለት የክስ አቤቱታው ውድቅ አድርጓል፡፡ የአሁን አመልካች ይህንኑ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ የቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ጥር 15/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተተ ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ከሟች ጋር በትዳር ስንኖር በቤቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ስለማድረጋቸው ተከራክረው ሳለ ኑዛዜው የአመልካች ድርሻ ያካተተ ስለመሆኑ አለመሆኑ በምስክሮች ሳይጣራ ቤቱ ለ1ኛ ተጠሪ በኑዛዜ ስለተላለፈ እና ስም ስለዞረ ብቻ የአመልካች የድርሻ ጥያቄ ውድቅ የመደረጉ አግባብነት በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

በዚሁ መሰረት 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 08/2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የላቸውም፣ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ሰነዶች ማረጋገጫ ፅ/ቤት የካቲት 08/1996 ዓ.ም ቀርቦ የተመዘገበ እና የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 881 መስፈርቶችን የሚያሟላ በመሆኑ ጉድለት የሌለበት ከመሆኑም በላይ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/187492 የኑዛዜ ይፍረስልኝ ክስ አቅርበው በክርክር ላይ ያለ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ተገቢነት የለውም፤ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስም በፍ/ብ/ህ/ቁ 973፣ 974፣ 1000 እና 1845 መሰረት በይርጋ ይታገዳል፤ የቤቱ ስም ሀብትም ወደ 1ኛ ተጠሪ በሚዛወርበት ወቅት አመልካች በየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት ፅ/ቤት በአካል ቀርበው የፈረሙ ከመሆኑም በላይ ቤቱም ሟች ወላጅ አባቱ ከወላጆቹ በውርስ ያገኙት በመሆኑ ክሱ አግባብነት የለም፤ አመልካች በቤቱ ውስጥ እንዲኖሩ የፈቀድኩትም 1ኛ ተጠሪ ነኝ፤ ቀደም ሲል ሌሎቹ 5ኛ ፣ 7ኛ ፣ 8ኛ እ 9ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት የኑዛዜ ይሻርልኝ በሚል በመ/ቁ 168981 እና በመ/ቁ 179266 ውድቅ የተደረገ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ፀንቶ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይግባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ደግሞ ግንቦት 08/2015 ዓ.ም በጋራ በተጻፈ መልስ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ዳኝነት ድርሻ ይለይልኝ የሚል ሆኖ አሁን ባቀረቡት አቤቱታ ላይ እና ማስቀረቢያ ነጥብ

ላይ ጥያቄው ከድርሻ ይለቀቅልኝ ወደ ኑዛዜ ይሻርልኝ የተቀየረ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ከሞላ ጎደል ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ 4ኛ፣ 5ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ግንቦት 08/2015 ዓ.ም በጋራ በተፃፈ መልስ የአመልካችን መከራከሪያ በመደገፍ የስር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ የአመልካች የሚትነት ድርሻ ሊለይላቸው ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በሌላ በኩል 6ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች በተደረገላቸው የጋዜጣ ጥሪ መሰረት ቀርበው መልስ ያልሰጡ በመሆኑ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡ አመልካችም ኑዛዜው እንዲሻርላቸው ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉን እና አሁን ከቀረበው ክርክር ጋር ተያያዥነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት የክስ አቤቱታ ከባለቤታቸው አቶ ፈለቀ ፈይሳ ጋር ከ1953 ዓ.ም ጀምሮ በትዳር ሲኖሩ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥጥ 103 የሆነውን ሶስት ክፍል የጭቃ ቤት ሙሉ በሙሉ አፍርሰው አንድ ሳሎን፣ ሁለት መኝታ ቤት፣ አንድ እቃ ቤት እና መፀዳጃ ቤት በበሎኬት በስፋት እና ይዘት ቀድሞ ከተሰራው የተለየ ቤት እና ሰርቪስ ቤቶችን ሰርተው እስክ አሁን ድርስ በይዞታቸው ስር አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን፤ ባለቤታቸው ካረፉ በኋላ ሚስትነታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/1681/2002 ላይ የካቲት 03/2002 ዓ.ም ያረጋገጡ መሆኑን፤ ከሟች ህልፈት በኋላ ተጠሪዎች የሟች የውርስ ሀብት እንዲለይላቸው ይጠይቃሉ ብለው ቢጠብቋቸውም ያልጠየቁ መሆኑን በመጥቀስ ከተጠቀሰው ቤት ላይ የሚስትነት ድርሻቸው እንዲለይላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ንብረቱ በኑዛዜ ከሟች አባታቸው የተላለፈላቸውና ኑዛዜው የጸደቀ መሆኑን በመጥቀስ ያቀረቡትን ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች በመቀበል ክርክር የቀረበበትን ቤት አስመልክቶ ሟች የካቲት 02/1996 ዓ.ም በቁጥር 660/7/96 በተመዘገበ ግልፅ ኑዛዜ 1ኛ ተጠሪ አስተላለፍው በዚሁ መነሻነት የቤቱ ስም ሃብት በተጠሪ ስም ዞሮ በካርታ ቁጥር የካ/207928/10 ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ ቤቱ የተላለፈበት ኑዛዜ ባልፈረሰበት እና ፀንቶ ባለበት አመልካች በጠየቁት መሰረት የድርሻ ክፍፍል የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም በማለት የክስ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ወስነዋል፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ንብረቱ ላይ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ ድርሻቸው እንዲለይ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን በንብረቱ ላይ ሟች ባለቤታቸው አቶ ፈለቀ ፈይሳ ለ1ኛ ተጠሪ ኑዛዜ ያደረጉ ስለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17058 /በቅጽ 04 እንደታተመ/ ፣ በመዝገብ ቁጥር 146503 /በቅጽ 23 እንደታተመ/ በሰጠው ትርጉም ኑዛዜው በፍርድ ቤት ውሳኔ መጽደቁ ሆነ የኑዛዜ ወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ መሰጠቱ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ እንደተሰጠ የማያስቆጥር እና ንብረቱ ላይ ክርክር እያደረገ ያለው ፍርድ ቤት ከሳሽ የሆነው ወገን በንብረቱ ላይ ያለው መብት ወይም ድርሻ ምንድን ነው፣ ኑዛዜው ድርሻ እየጠየቁ ያሉ ሰዎችን ጨምሮ ሊያስተላልፍ ይችላል ወይስ አይችልም፣ የሌላ ሰው ድርሻ ካስተላለፈ ሕጋዊ ውጤቱ ሆነ የኑዛዜው ተፈጻሚነት ምን ሊሆን ይችላል የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ በመመርመር ሊወሰን እንደሚገባ ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ክስ ባቀረበቡት ንብረት ላይ ድርሻ ያላቸው መሆን አለመሆኑን፣ ድርሻ ካላቸው ኑዛዜ የአመልካችን ድርሻ ጨምሮ ማስተላለፉ ያለውን ሕጋዊ ውጤት በጭብጥነት በመያዝ ሊመርመር ሲገባ ኑዛዜው ጸንቶ ያለ በመሆኑ የአመልካች ክስ ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የጸፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት ክርክር የሚስትነት ድርሻ ይለይልኝ ክሱ ውደቅ ከተደረገ በኋላ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 187492 የኑዛዜ ይሻርልኝ ክስ አቅርበው አቤቱታው በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ መወሰኑን ጠቅሰው አቅርበዋል፡፡ ይሕ ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የተፈጠረ አዲስ ክርክር በመሆኑ፣ አመልካች ለተከሰተው አዲስ ውጤት የሚያቀርቡት ክርክር ሊሰማና የመደመጥ መብታቸው መከበር ያለበት ስለሆነ እና አዲስ የተከሰተው ነገር አመልካች ያቀረቡት የድርሻ ይለይልኝ ክስ ላይ ያለው ውጤት ክርክር ተደርጎበት የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ በሰበር ችሎቱ ደረጃ መመርመር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በጭብጥነት በመያዝ ግራቀኙን አከራክሮ ኑዛዜ ይሻርልኝ የሚለው ክስ በይርጋ የታገደ ነው መባሉ አመልካች ላቀረቡት ድርሻ ይለይልኝ ክስ ያለው ወጤት ምንድን ነው፣ ኑዛዜ ይሻርልኝ ክሱ የቀረበው ድርሻ ይለይልኝ ክስ ከቀረበ በኋላ መሆኑ ምን ውጤት ያስከትላል፣ በአመልካች ድርሻ ላይ ኑዘዜ ተደርጎ ከሆነ ውሳኔው ድርሻቸው እንዳይለይ የሚያደርግ መሆን አለመሆኑን በመመርመር ውሳኔ ሊሰጠበት የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 298465 ሕዳር 20 ቀን 2015 ዓ/ም እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 177612 ሐምሌ 29 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርዱ የተለዩት ጭብጦች ላይ ግራቀኙን በማከራከር እንዲሁም በ1ኛ ተጠሪ በሥር የቀረቡ ሌሎች መቃወሚያና ክርክሮችን ተመልክቶ በሕግ መሠረት እንዲወሰን ጉዳዩን በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሰረት መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- የሥር ፍርድ ቤቶች መዝገቦች ይመለሱ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የልዩነት ሀሳብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስሜ በአራተኛ መስመር ላይ የተሰቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበውን ጉዳይ በድጋሚ እንዲጣራ ለስር ፍርድ ቤት በመለሰበት ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማሁ በመሆኑ የልዩነት ሀሳቤን በሚከተለው መልኩ አስፍሬያለሁ፡፡

ከክርክሩ አመጣጥ መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች የሚስትነት ድርሻዬ ይለይልኝ በሚል ክስ ያቀረበበትን ቤት ሟች ለአሁን 1ኛ ተጠሪ በኑዛዜ ያስተላለፈ ለመሆኑ አመልካች ጭምር የካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይኸው ቤቱ የተላለፈበት ኑዛዜ ፀንቶ ባለበት አመልካች በቤቱ ከላይ የድርሻ ይለይልኝ ጥያቄ ሊያነሱ አይችሉም በሚል ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህንኑ ተከትሎም የአሁን አመልካች ኑዛዜውን ለማስሻር በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/187492 ላይ አቅርበውት የነበረው ክስ ውድቅ የተደረገ መሆኑ በክርክር ሂደት በመገለፁ ይኸው የኑዛዜ ይሻርልኝ ክርክር የተከናወነበት ዋናው መዝገብ ከስር ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ተደርጎ ችሎቱ መርምሮታል፡፡

በዚሁ አግባብ አመልካች የሚስትነት ድርሻቸው እንዲለይላቸው ያቀረቡት ክስ ኑዛዜው ሳይሻር ሊቀርብ አይችልም ተብሎ ውድቅ መደረጉን በምክንያትነት ጠቅሰው ኑዛዜው በሚስትነት ድርሻዬ ላይ ጭምር የተደረገ በመሆኑ ሊሻር ይገባል በሚል በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው የነበረ መሆኑን፣ ፍርድ ቤቱም የቀረበው ክስ ላይ የአሁን 1ኛ ተጠሪን መከራከሪያ ከሰማ በኋላ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የተላለፈበት ኑዛዜ በ2002 ዓ.ም የሟች ውርስ በሚጣራበት ወቅት ኑዛዜው ሲነበብ አመልካች በቦታው የነበሩ ስለመሆኑ ከሰው ምስክር እንዲሁም ሚስትነታቸው እና የአሁን 1ኛ ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽነት በተረጋገጠበት የፍርድ ቤት ውሳኔ ያረጋገጠ መሆኑን ወራሽ ያልሆነ ሰው ኑዛዜ እንዲሻርለት የሚያቀርበው ክስ ሊቀርብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ አስመልክቶ በህግ ተለይቶ ያልተቀመጠ በመሆን በዚሁ መሰረትም አመልካች በ2002 ዓ.ም ኑዛዜው ሲነበብ በቦታው የነበሩ ሆኖ ከ10 ዓመት በኋላ ኑዛዜውን በመቃወም ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት አቤቱታቸውን ውድቅ ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ያፈራውን ንብረት ወይም ያለውን መብት ከህልፈቱ በኋላ ምን መሆን እንዳለበት የሚወሰንበት እና በህግም ጥበቃ የሚደረግለት ህጋዊ ተግባር ነው፡፡

የኑዛዜ ቃልም ከተናዛዡ ህልፈት በኃላ የተናዛዡን ትክክለኛ ሀሳብ ሚገልፅ ብቸኛ ማስረጃ ነው፡፡ ኑዛዜው በዚህ መልኩ ህጋዊ ውጤት ይኖረው ዘንድ ጉድለት የሌለበት ፈቃድ የተገለፀበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከመሆኑ በተጨማሪ ለህገዊነቱ በህግ በግልፅ የተመለከተውን መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡

ከኑዛዜ ህጋዊነት ጋር በተያያዘ የፍትሓ ብሄር ህጉ ሶስት መመዘኛ ሁኔታዎችን አስቀምጧል፡፡ እነዚህም የሥር ነገር ሁኔታዎች፣ የኑዛዜዎች ፎርም እና ማስረጃ እንዲሁም ስለኑዛዜዎች መሻር እና ውድቅ መሆን ሚሉት ስለመሆናቸው ከፍ/ብ/ህጉ ቁጥር 857 እስከ 908 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የኑዛዜው የሥር ነገር መመዘኛ ሁኔታዎች ከቁጥር 875 እስከ 880 በዝርዝር የተመለከቱት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጠ አንዱ ሟች ያደረገው ኑዛዜ ሊፈፀም የሚችል መሆን ይኖርበታል በሚል በቁጥር 865 ስር የተመለከተው ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ኑዛዜ አንድ ሰው በራሱ መብት እና ንብረት ላይ ከህልፈቱ በኃላ የሚያዝበት ህጋዊ ተግባር ነው ፡፡ ድርጊቱ ህጋዊ ነው ተብሎ በህግ ጥበቃ ለማድረግ ደግሞ ኑዛዜው በእርግጥም በተናዛዡ መብት እና ጥቅም ላይ ብቻ የተደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ አገላለፅ አንድ ሰው በሌላ ሰው ንብረት/መብት/ ላይ ኑዛዜ ቢያደርግ ኑዛዜው ህጋዊ ውጤት አይኖረውም ማለት ነው፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 865 ስር ሟች የተወው ኑዛዜ ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ሊሆን አይገባም በማለት የተደነገገውም እንዲህ ዓይነት ድርጊትን ለመከላከል ታስቦ እንደሆነ መገንዘብ የቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች የሚስትነት ድርሻዬ ይለይልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ የተደረገው ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት የተላለፈበት ኑዛዜ ፀንቶ ባለበት ጥያቄው ሊነሳ አይቻልም በሚል ነው፡፡ ከዚሁ በኃላ አመልካች ኑዛዜውን ለማስሻር ያቀረቡት ክስ ከላይ በተመለከተው ምክንያት በይርጋ ውድቅ ተደርጓል፡፡ ኑዛዜውን ለማስሻር አመልካች ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ለማድረግ ፍርደ ቤቱ የጠቀሰው ምክንያት እና የደረሰበር ድምዳሜ አግባብ መሆን አለመሆኑ ጉዳዩ የክርክር መስመሩን ጠብቆ በቀረበ ጊዜ የሚታይ ይሆናል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ግን አመልካች የሚስትነት ድርሻዬ ሊለይልኝ ይገባል በማለት ክስ ያቀረበቡትን ንብረት ባለቤታቸው ባተረፉት ኑዛዜ ለአሁን 1ኛ ተጠሪ ተላልፈሮ መብት ጭምር የተፈጠረበት ከመሆኑም በላይ ንብረቱ የተላለፈበትን ኑዛዜ ለማስሻር አመልካች ያቀረቡት ክስ ተቀባይነትን ያጣ በመሆኑ ኑዛዜ አሁንም ጭምር በፍርድ ቤት ውሳኔ የፀና መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የንብረቱ አስረተላለፍ ህጋዊ ነው ሚባል ከሆነ ደግሞ አመልካች ኑዛዜውን ለማስሻር ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ አስመልቶ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የክርክር መስመሩን ጠብቀው ከሚያስለውጡ በቀር ውሳኔው ፀንቶ ባለበት ድርሻዬ ሊለይልኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩበት ህጋዊ መሰረት የለም፡፡ ኑዛዜውን አስመልክቶ ጠተሰጠው ውስኔ ህጋዊነትም ቢሆን የሙግት ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ስልጣን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ባለው የበላይ  ፍርድ ቤት ከሚመረመር በቀር በሌላ ክርክር መነሻነት በተመሳሳይ እርከን ላይ በሚገኝ ፍርድ  ቤት እንዲመረመር ነደረጉ ሥነ ሥርዓታዊ ነው ሚል እምነት የሌለኝ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ጉዳዩ ለስር ፍርድ ቤት  ሊመለስ አይገባውም ነበር ፡፡

በመሆኑም አሁን ባለው ይርክር ደረጃ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት የሚያስችል  ምክንያት  ባለመኖሩ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ለዚህ  የሰበር አቤቱታ መሰረት የሆነው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል ነበር በማለት  ከስር  ባልደረቦቼ የተለየ አቋም ይዣለሁ ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !